# ከጋሻ ለኢትዮጵያ

## Gasha for Ethiopia

(የዶ/ር ጥላሁን ገሠሠን በሞት መለየት አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ)



የሙዚቃ ንጉሥ እየተባለ በኢትዮጵያ ህዝብ ሲሞገስ የኖረው ተወዳጁ ከያኒ ጥላሁን ገሠሠ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት በጋሻ ለኢትዮጵያ አባላት ዘንድ መሪር ሀዘን ፈጥሯል።

ከግማሽ መእተ አመት በላይ በተስረቅራቂ ድምፁ ድፍን አገሩን በሰላም ጊዜ ሲያዝናና፣ በፈታኝ ወቅት ደግሞ የህዝቡን እና የጦር ኃይሎቻችን ሞራል ሲገነባ የኖረው ጥላሁን በድንገት በሞት መለየቱ ለቤተሶቦችና ለቅርብ ወዳጆቹ ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ ሀዘን ያስከተለ ሆኗል።

ይህ ዘመን የማይተካው ታላቅ የጥበብ ሰው ለወገኑና ለአገሩ እንደኖረ በህይወቱ እያለ ያሳተማቸው ከ400 በላይ የሙዚቃ ስራዎቹ በጉልህ ይመስክሩለታል።

ታላቁ የሙዚቃ አባት ጥላሁን ገሠሠ በአካል ቢለየንም በመንፈስ ግን በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ እንደሚኖር፤ አስደናቂ ሥራዎቹም ለዘመናት ብሄራዊ ቅርስ ሆነው ጥላሁንን ህያው እንዳረጉት ይኖራል።

ጥላሁን ላዜመላቸው ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ክብር፣ ታሪክ እና ሰንደቅ አላማ እኛ የጋሻ ለኢትዮጵያ አባላትም ከኢትዮጵያ ህዝብ ጎን ቆመን ለዓላማዎቹ መሳካት የበኩላችንን አስተዋጽኦ እንደምናደርግ በዚሁ አጋጣሚ ቃልኪዳናችንን እናድሳለን።

የዚህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ በሞት መለየት ሀዘኑ ለጠናባቸው ለቤተሰቦቹ፣ ለቅርብ ዘመዶቹና ጋደኞቹ፣ ለስራ ባልደረቦቹ እና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ መጽናናትና ብርታቱን እንዲሰጥልን ፀሎታችን ነው።


ጋሻ ለኢትዮጵያ
ዋሽንግተን ዲሲ


April 26, 2009


Gasha for Ethiopians Civic Association
www.ethiopiangasha.org/
admin@ethiopiangasha.org